Region Västernorrland

# ልጅ ሲታመም - መረጃ ለወላጆች

När barnet är sjukt – föräldrainformation

ልጆች ብዙ ጊዜ ይታመማሉ። በ0-4 ዓመት ዕድሜ ገደማ የሚገኙ ልጆች በዐመት ባማካይ ከ6-8 ጊዜ የመተንፈሻ ኢንፌክሽን ይይዛቸዋል። እነዚህ ኢንፌክሽኖች ልጆች በሽታ የመከላከል ዐቅማቸው እንዲጎለብት ያግዛሉ። በልጅ ቡድኖች የኢንፌክሽኖች መተላለፍ ፈጽሞ ማስወገድ አይቻልም፤ ቢሆንም መጠኑን መገደብ ይቻላል። እንደ ወላጅ መጠን: ልጅ ኢንፌክሽን ሲይዘው ፈጽሞ እስኪድንና ወደ ሌሎች ልጆች የማስተላለፍ አደጋ ለመቀነስ በመንፈቀ-ዐመት ብዙ ጊዜ እቤት ቀርቶ የታመመ ልጅን ለመንከባብ የግድ ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል።

ልጁ ወደ አፀደ-ህፃናት እንዲሄድ ወሳኙ የልጁ ጠቅላላ የጤና ሁኔታ: ማለትም በተለያዩ የትምህርት እንቅስቃሴዎች የመሣተፍ ፍላጎቱ ነው። እንደ ወላጅ መጠን: ልጁ ተጽኖ እንዳለው እቤት ሆኖ ምናልባት ሁሌ መገንዘብ ኣይቻልም ይሆናል። ልጁ ባፀደ-ህፃናቱ ከሌሎች ልጆችና አዋቂዎች መካከል በሚገኝበት ወቅት ግን ልጁ እንደ ተለመደው ፍላጎት እንደሌለው ሠራተኞቹ ወድያውኑ ለይተው ያውቃሉ። ልጁ ድካም ቢሰማው፣ ካልበላ/ካልተኛ፣ ትኩረት ከሌለው ወይንም በሌላ መንገድ ፍላጎት እንደሌለው ካሣየ: ወላጆቹ በተቻለ መጠን በቶሎ መጥተው ወደቤት ቢወስዱት ይሻላል። ሠራተኞቹ ልጁ እንዴት እንደሚሠራ ጠባዩና ኣግባቡ እንዴት እንደሆነ የማወቅ ልምድ ስላላቸው: በልጁ ጠቅላላ የጤና ጥርጣሬ ከተነሣ የነሱ ግምገማ ወሳኝ ነው።
ወላጆች ልጁ ወደ አፀደ-ህፃናት ይሄድ አይሂድ እርግጠኛ ካልሆኑ: ወደ አፀደ-ህፃናቱ መደወል ይችላሉ። የህክምና ምክር ከተፈለገ ወደ ጤና ጥበቃ ማእከል ወይንም 1177 ይደውሉ።

# ልጅ ወደ አፀደ-ህፃናት ሳይሄድ እቤት የሚቀርባቸው መመሪያዎች:-

- *ልጁ ትኩሳት ሲይዘው።* ልጁ ወደ አፀደ-ህፃናት ከመመለሱ በፊት: ትኩሳቱ ከተወው በህዋላ (ፀረ-ትኩሳት መድኃኒት ሳይወስድ) ቢያንስ ለ24 ሰአታት እቤት ይቁይ።
- *ልጁ ድካም ሲሰማው።* ልጁ ከድካም የተነሣ ባፀደ-ህፃናቱ የተለመዱ እንቅስቃሴዎች መሣተፍ ቢያቅተው: ለምሣሌ በሳል ምክንያት እንቅልፍ ካጣ: ከልጁ ጋር እቤት ይቆዩ።
- *ተቅማጥ ሲይዘው/ሲያስታውከው።* ትውከት ከተወው: ሰገራው እንደ ውሀ ቀጭን መሆን ሲያቆምና ልጁ በደንብ መብላት ከጀመረ በህዋላ ቢያንስ ለ48 ሰአታት ከልጁ እቤት ይቆዩ።
- *ሌላ ተላላፊ በሽታ ሲኖረው* ለምሣሌ እንደ ኢምፐቲጎ (svinkoppor)። ቁስሉ እስኪደርቅ እቤት ይቆዩ።
- *የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒት (አንቲብዮቲካ) ሲወስድ።* የልጁ አጠቃላይ የጤና ሁኔታ: ትኩሳት እስኪሻሻልና ህክምናው ቢያንስ ለሁለት ቀናት እስኪሠጥ እቤት ይቆዩ። አንቲብዮቲካና ሌሎች ጊዜያዊ መድኃኒቶች በወላጆች ናቸው የሚሠጡት።

በተወሠኑ ጊዜያት የመብላትና በደንብ የመተኛት ልምዶች ለልጆች ጤና አስፈላጊ ናቸው። የአካል እንቅስቃሴ: ከተቻለ እቤት ውስጥ: ልጆቹን ያዝናናል ጤናም ይሠጣል። እንደ ብርድ ልብስ፣ ኣሻንጉሊቶች የመሣሠሉት ወደ አፀደ-ህፃናት የሚወሰዱ ዕቃዎች የሚታጠቡ መሆን አለባቸው።

የእጅ ጽዳትና ሲስሉ/ሲነጠሱ አፍን የመከደን ልምዶች: ከአፀደ-ህፃናቱ የጽዳት ምክሮች ጥቂቶች ናቸው። ያፀደ-ህፃናቱ ሠራተኞች በልጆቹ መካከል ያለው የኢንፌክሽን ሁኔታ የተሟላ ስዕል አላችው፤ እና የጽዳት ልምዶቹን ትንሽ ጠበቅ ማድረግ ካስፈለገ ውሣኔ ይሠጣሉ።

### ለተጨማሪ መረጃ

- ለምሣሌ ልጆች ጉሮሮአቸው ውወይ ጆሮአቸው ሲያማቸው ምን እንደሚደረግ በ www.1177.se ይመልከቱ።